# ተስፋየ ተስፋ ሲቆርጥ

(ሰናይ ገ/መድህን)
ክፍል 4



*ኢትዮጵያዊ ኤርትራዊ ጋዜጠኛ ሰናይ ገ/መድህን*

ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ በቴሌቪዥን ቀርበዉ (የቀጥታም ሆነ የተቀረፀ) ቃለምልልስ ከማካሄዳቸዉ በፊት ቀደም ብሎ በቴሌቭዥንና ራዲዮ ተደጋጋሚ ማስታዎቂያ መልቀቅ የተዘወተረ ነዉ፡፡ በተለይም ቃለምልልሱ የሚደረገዉ ከዉጭ ከሚመጡ ጋዜጠኞች ጋር ከሆነ ማስተዋወቁ ሞቅ ደመቅ ይላል፡፡ ጋዜጠኞቹ

በቀጠናዉና ዓለምአቀፉ የወቅቱ የፖለቲካ ትኩሳት ጉዳይ ትንታኔ ፍለጋ ሰዉየዉ ጋ እንደሚመጡ ተደርጎ ይራገባል፡፡ያሳብቅማልም፡፡



*የቂምና የጥላቻ ደራሲ፣ የሻቢያው ሰላይ ተስፋዬ ገ/አብ*

ያዉ 15ዓመት እንዳራገብኩላቸዉና እንደታዘብናቸዉም ሰዉየዉ ለመተንተን ወደሁዋላ አይሉም፡፡ ይደፍራሉ፡፡ ካፈርኩ አይመልሰኝ ወይንም የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም እንዲሉ ነገር ፡፡ የአንድ ሰሞኑ የቅድመ ቃ/መ ማስታወቂያ ታዲያ ይበልጥ ትኩረትን የሳበ ሆነ፡፡ ታዋቂ ከሆኑት ኢትዮጵያዊያን ድረገፆች መሀል ከኢትዮጵያን ሪቪዉ ጋር ቃለምልልስ የማካሄዳቸዉ ጉዳይ ፡፡ በኤርትራ ቆይታየ ሰዉየዉ ኢትዮጵያዉያን ተቃዋሚ ግለሰቦችን በተናጥል ከማነጋገር በቀር ከኢትዮጵያዉን ሚድያዎች ጋር ፊትለፊት ቁጭ ብለዉ አያዉቁም፡፡ ያን ጊዜ ግን በራቸዉን ለሚዲያዎች ክፍት ያደረጉ መሰሉ፡፡ ዳሩ ግን በኢትዮጵያን ሪቪዉ ለመቅረብ በፈለጉበት ጊዜ አንድ ነገር ግልፅ ነበር ፡፡ መገምገም ለቻለ፡፡

ይሄዉም ኤርትራ ከመሸጉት ኢትዮጳያዉያን ተቃዋሚ ሀይሎች መሃል የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዴምህት) እየጎለበተ መሄዱና የሌሎቹ የመፍተልተል ጉዳይ አደባባይ መዉጣቱ፤ በተለይም በኤርትራ ከዴምህት አራት አመት በፊት ቀድሞ ግንባር ሆኖ የተመሰረተዉ የኢትዮጵያ ህዝቦች አርበኞች ግንባር እንደግመል ሽንት የሁዋሊዮሽ መዝረክረኩና (ስለመረጥኩት ቃል ይቅርታና በግንባሩ ለተሰዉ ለታገሉ ለሚታገሉና ለሞከሩ ሁሉ አክብሮቴን እየገለጥኩ የሁዋሊዮሽ መፍተልተሉ ማለቴ የግንባሩን ጉዞ ይሆናል) መወነጃጀሉ ይፋ እየሆነ መሄዱን ይጠቅሱዋል፡፡ የኤርትራ መንግስትም ከሚወነጀሉት ዋነኛዉ በመሆኑ፡፡ በኢትዮጵያዉያን ሚድያ ቀርበዉ ካንገት ይሁን ካንጀታቸዉ ቢያስተባብሉ ምንም እንደማይከስሩ በመካሪዎች ተመከሩ እንበል፡፡ እንዲያዉም ጥቂት የዋሆችን ለወያኔ ማሰፈራሪያነት ልንማርክ እንችላለን ይባሉም ይሆናል፡፡ ባናቱ ላይ ስለኢትዮጵያና ህዝቡዋ የሚሰጡት ገመድ ትንታኔ አለ፡፡ እናም ቃለምልልሱ ተካሄደ ፡፡ግንባሮቹም ቀጠሉ፡፡ላሁኑ ይሄዉ ይበቃናል፡፡

ፕሬዚዳንቱ ቃለምልልሱን ያካሄዱት እንደሚታወሰዉ ከሁለት ጋዜጠኞች ጋር ነበር ፡፡ ከኤልያስ ክፍሌና ከሎንዶኑ ስለሺ ጥላሁን ጋር፡፡ በድረገፅ በስም ብቻ ከማዉቀዉ ከኢትዮጵያን ሪቪዉ ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ ጋር የተዋወቅሁትም በዚሁ ጊዜ ነበር፡፡ ከስለሺ ጋር ቀደም ባለ ጉብኝቱ ተዋዉቀናል፡፡

ከጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ ጋር በተለያዩ ጥቂት አጋጣሚዎች በኤርትራ በኩል ስለሚደረጉ የትጥቅ ትግል አያያዞች ጉዳይ የሀሳብ ልዉዉጥ ያደረግን ሲሆን የኔ ድምዳሜ "ከንቱ ልፋትና መስዋዕትነት መክፈል ነዉ" የሚል ነበር፡፡ አሁንም ፡፡ ዝርዝር እማኝነቴ አሁን አያሻንም፡፡ ኤልያስ በህግደፍ ተስፋ ሰንቆ ነበር የመጣዉ፡፡ እንደተረዳሁት፡፡ ከፕሬዚዳንት ኢሳያሳ ጋር ቃለምልልስ ካካሄደ በሁዋላም በቀጠሮ ኒያላ ሆቴል ተገናኝተን በሙያዊ የስራ ዕቅዱ ዙሪያ ያሰቡትን ሲገልጥልኝ ከዚሁ ተስፋ የመነጨ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ፡፡ እናም ፀረ ወያኔ የትጥቅ ትግሉን በቅርብ ለመደገፍና መረጃዎችን በቅርብ ለማስተላለፍ የኢትዮጵያን ሪቪዉ ቢሮ በአስመራ ለመክፈት እንቅስቃሴ መጀመሩንና በዚህ ቢሮም ተስፋየ ገብረአብና እኔን እንድንሰራ እንደሚፈልግ በመግለጥ ግብዣዉን አቀረበልኝ፡፡ ስለ ህግደፍና አርበኞች ግንባር ብዙ አሉታዊ ነገሮች ይፋ በወጡበት ጊዜ ኤልያስ ይህን እቅድ ማሰቡ ትንሽ ግራ አጋባኝ፡፡ ምን ተማምኖ ነዉ በሚል።፡"እርግጠኛ ነህ ይሄ ነገር ይሳካል?" የግል ሚዲያ የማይዋጥላቸዉ ኢሳያስ ጉያቸዉ ዉስጥ ያዉም የአማርኛ ድረገፅ እንዲከፈት ቀና ሊሆኑ? ነባር የህግደፍ ታጋዮችና የኢሳያስ ህቡዕ ፓርቲ አባላት (ኤማሰ) የሚቆጣጠሩት የአማርኛዉ ኦሮሚኛ ትግራይና ሶማሌኛ ቴሌቭዥንና ራዲዮ ፕሮግራሞች እንዴት በሽምቀቅ እንደምንሰራ እያወቅኩ እነኤልያስን በነፃ ሚዲያነት እንዲሰሩ እንዴት ይፈቅዳሉ ብዬ ልገምት?.... ፡፡ ኤልያስ ጥርጣሬየን ተገንዝቦ "እነ ኮ/ሎኔል ፍፁም በኢትዮጵያዊያን ተቃዋሚዎች አያያዝ ላይ ብዙ ነገሮችን እንዲያስተካክሉ ተነጋግረናል፤ በአጠቃላይ ፕሬዚዳንቱም አይዞዋችሁ ብለዉናል" ሲል ያገኙትን ተስፋ ባጭሩ አመላከተኝ፡፡

ቢሳካም ባይሳካም ለእሺታየ አላቅማማሁም፡፡ ምክንያቱም የሁዋላ የሁዋላ እጅ እጅ እያለኝ ከመጣዉና የማላምንበትን እየሰራሁ በመሆኔ ህሊናየ እኔነቴን ሲጠየፈዉ እየታወቀኝ ከሄደዉ የኤርትራ ማስተወቂያ ሚ/ር ጭፍን ፕሮፓጋንዳ አካባቢ መገላገያ አገኘሁ በማለት፡፡ አንድ ከባድ ችግር ግን ነበረ፡፡ በግል ፍላጎት ለመልቀቅ አይፈቀድልኝም፡፡ ስለዚህ ኤልያስ በዋነኛነት እንዲያነጋግር ተስማማን፡፡ ለሱ ሲሉ

ሊፈቅዱ ይችላሉ በሚል፡፡ ሌላዉ ያሳሰበኝ ደግሞ የሙያ ችሎታየ ጉዳይ ነዉ፡፡ በድረገፅ ጋዜጠኝነት የመስራት ልምዱ የለኝምና፡፡ ቢሆንም ከኤልያስና ተስፉየ እማራለሁ ስል ተስፋ አደረግኩ፡፡

ከኤልያስ ጋር ከተነጋገርኩ በሁዋላ ተስፋየን ለማነጋገር ቸኮልኩ፡፡ የደራሲዉ ማስታዎሻን ያዘጋጅ በነበረበት ሰሞን በመሆኑ የኒያላ ሆቴል ቋዋሚ ተሰላፊ ነበር፡፡ "እህሳ የኤልያስን ሃሳብ እንዴት አገኘኸዉ?" እንደተገናኘን ያቀረብኩለት ጥያቄ ነበር፡፡ የሹፈት ሳቁን አስቀደመና "አንተ ምን አልከዉ?" ጥያቄየን በጥያቄ መለሰ፡፡ እኔማ "በኔ በኩል ደስተኛ ነኝ፣ በአለቆቼ በኩል ግን አንተ ግፋበት" በሚል ተነጋግረናል "ባንተ በኩልስ ሃሳብህ ምንድን ነዉ ?" የሰጠኝን ምላሽ አልጠበቅኩም። "ለግለሰብ ተቀጥሬ ልሰራ? አላደርገዉም፡፡ ለነገሩ "ሥራ አስኪያጅ ትሆናለህ ብሎኛል ግን አይመቸኝም" አለኝና አረፈዉ፡፡ ምነካዉ ልጄ? በሚል በዉስጤ ብዙ ጥያቄዎች አመላለስኩ፡፡ ግና በዉስጤ ይገፔ "እና እንደዚህ ብለህ ምላሽ ሰጠኸዉ?" "ለሱማ ግዴለም እሺ ብየዋለሁ" ግራ በሚያጋባዉ ባህሪዉ እየተገረምኩምና ፊትለፊት አለመፈለጉን ቢገልፅለትስ ምን ነበረበት በሚል ስሜት ተሞልቼ "እንግዲህ እንደምታዉቀዉ ያለሁበት ቦታ 15 ዓመት ሰራሁ አሁን ደግሞ ይሄን እድል ካገኘሁ ለለዉጥም ራሴን ለማስተማርም ይረዳኛልና አለቃየን (የዉጭ ክፍል ዳይረክተሩን አቶ መኩሪያ ወልዱን) እንደሁኔታዉ አናግረዋለሁ፡፡" ስል በድጋሚ ዉሳኔየን ገለጥኩለት፡፡ "ኖኖኖኖ ፍላጎትህን አትግለጥ መልቀቂያም አትጠይቅ " ተስፋየ እንደምክርም እንደማስጠንቀቅም ሰነዘረ፡፡ እረ አንባረቀብኘ ነዉ የሚባለዉ፡፡ "እንዴ ለምን? ይሆናል ወይንም አይሆንም ነዉ የሚሉት" እየገረመኝ መለስኩለት፡፡ "አርፈህ ስራህን ስራ የኤልያስ የሚሳካ አይደለም" እቅጩን ነገረኝ፡፡ "ከፕሬዚዳንቱ ጋር ተነጋግሩዋል ከእኛ ሃላፊዎችም ጋር በተደጋጋሚ ተወያይቶ ነዉ እኔንና አንተን ለስራዉ የጋበዘን፡፡ ማለቴ ቢሮ መከፈቱን በተመለከተ ከነሱ ፈቃድ እዳገኘ ታዉቃለህ አነጋግሮሃል አሁን እንዴት አይሳካም ትላለህ?" ስል ወጥሬ ጠየቅኩት፡፡ እኔን ከኤልያስ ጋር እንዳልሰራ እያከላከለም መሰለኝ፡፡ "ዝም ብሎ ነዉ አይሳካም" ባጭሩ መለሰልኝ፡፡ ከዚህ በላይ መነጋገሩን አልመረጥኩም፡፡ ኤልያስ ከፕሬዚዳንቱና የበላይ ሀላፊዎች ጋር ተነጋግሮ የደረሰበትን ነገር ተስፋየ እንደማይሆን በእርግጠኝነት ሲነግርኝ በዝምታ ከመከታተል ዉጭ ሌላ ምንስ እላለሁ፡፡ለነገሩ የህግደፍ ሀላፊዎች በኢትዮጵያዉያን ተቃዋሚዎች ጉዳይ ላይ የሚያደናግር ዉሳኔዎችን እያስተላለፉ እርስበርስ ሲያናቁሩ ለመታዘብ የቻልኩባቸዉ አጋጣሚዎችን ስለማስታዉስ (አሁን አላነሳዉም) ይሄንንም በአርምሞ መከታተል መረጥኩ፡፡

የኢትዮጵያን ሪቪዉ የአስመራ ቢሮ ለመክፈት አሰፈላጊ የተባለዉ ሁሉ መስተንግዶ በፍጥነት ተጀመረ፡፡ ቢሮዉ ከኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ህንፃ ጎን (ፎርቶ) በሚገኘዉ ታችኛዉ ጊቢ ተመረጠ፡፡ የቢሮ እቃዎች አንድባንድ በመንግስት ወጪ ተገዝተዉም ከመጋዘንም እየተፈለጉ ገቡ፡፡ የቅርብ ሀላፊያችን ወዲያ ወዲህ ሲራወጥ አስተዉለዉ ያዝኩ፡፡ "ተስፋየ አይሳካም ያለዉ ነገር ዝም ብሎ ነዉ መሰል" አልኩ በተግባር የሚደረገዉን ዝግጅት እያየሁ፡፡ ግን አያሌ በጅምር የቀሩ የህግደፍ ተፍተፎችን አይቻለሁና ድምዳሜ ላይ አልደረስኩም፡፡ የቢሮ ዝግጅቱ በሚስጥር የተያዘ ነበር፡፡ እኔም ለአለቃየ ሳልናገርም እንደማያዉቅ ሆኜም ግን ማነፍነፌን ቀጠልኩ፡፡ በዚኑ ሰሞን ኤልያስ ወደ አሜሪካ መመለሱን ሰማሁ፡፡ እኔን በተመለከተ ከአለቆቼ ጋር ስለመነጋገሩ ሆነ ዉሳኔያቸዉን አስመልክቶ የሚነግረኝ ነገር ኖራል ብየ ጠብቄ ነበር ግን አልሆነም፡፡ ብዙ ጉዳዮች እንዳሉትና ሳንገናኝ ቢሄድም በቅርብ ተመልሶ ወደ አስመራ እንደሚመጣና እስከዚያ ግንኙነታችንን ለመቀጠል አድራሻዎች ተለዋዉጠን ተነጋግረን ነበር፡፡ አሜሪካ ከገባ በሁዋላ አልተገናኘንም፡፡በዚህ በኩል የቢሮ ዝግጅቱ አልቆ መጀመሩ ብቻ እንደሚጠበቅ አረጋገጥኩ፡፡ ሆኖም ቁሱም ዝም መፅሀፉም ዝም ሆነ፡፡

አንድ ሁለት ወራት በዝምታ አለፉ፡፡ አሁን መግለፅ የማያስፈልገኝ (ዝርዝሩ ሰፊ ነዉና) በኦነግ በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በደቡብ ኢ.ህ.ግ. በኦብነግ በአስመራዉ አልሸባብ አባላት መካከል የተለያዩ ፍፃሜዎች ተከሰቱ፡፡ ሰንበትበት ብሎም ሌላ አሳዛኝ ፍፃሜ ተከተለ፡፡ የኢ.ህ.አ.ግ. መስራቹና የመጀመሪያዉ አመራሩ የ14 ዓመት የልብ ወዳጄ ኮ/ል ታደሰ ሙሉነህ ደብዛዉ ጠፋ፡፡ በህግደፍ የፀጥታ ሀይሎች ከቤቱ ታፍኖ መወሰዱን ብናረጋግጥም የት እንዳስገቡት ማወቅ አልቻልንም፡፡ ወጣን ወረድን ታዴን የበላዉ ጅብ አልጮህ አለ፡፡ ልባችን ተነካ አዘንን፡፡ ታዴን የምናዉቅ ኢትዮጵያዉያንም ኤርትራዊያንም ፡፡ ይህ አይነቱ የአፈና ተግባር በኤርትራ የተለመደ ቢሆንም ታዴ ላይ ይህ ይፈፀማል ብለን አልጠበቅንም ነበርና፡፡ "ኮ/ል ታደሰን አሰሩት ይሄ ነገር እኮ ብዙ ነገር ያበላሻል"። በዚያኑ ሰሞን ከተስፋየ ጋር እንደተገናኘን ያነሳሁለት ያሳዘነኝና ያሳሰበኝ ጉዳይ ነበር፡፡ ካገኘሁት ጋር እንደማነሳዉ ቀዳሚ አሳሳቢ ጉዳዬ ነዉ ያነሳሁለት። ምናልባትም የሰማዉና የሚያዉቀዉ ነገር ይኖር ይሆናል በሚል፡፡ "ዶሮየ ጠፋብኝ" ያልኩትም አልመሰለዉ፡፡ ሌላ ጨዋታ ቀጠለ፡፡ አይመለከተኝም ዓይነት፡፡ ቢያንስ በጉዳዩ ዙሪያ አንድ ሁለት ማለት በቻለን ነበር፡፡ "የታዴን መታሰር የሚያወግዙ ኢትዮጵያዉያን ይኖራሉ …ግንኙነቶች ሊበላሹ ይችላሉ" የሚሉ የመሳሰሉ ርዕሶችን አንስተን ሀሳብ መለዋወጥ በቻልን ነበር ፡፡የሁለቱም አገሮች ህዝቦች ግንኙነት በጋራ ይመለከተናል ብዬ በማመኔም ነበር፡፡ ስለእስሩ ቦታና ሁኔታ የሚያዉቀዉ ነገር ባይኖርም ወይንም መደበቅ ቢፈልግም እንኳዋን ሀሳብ መለዋወጡ ምን ነበረበት? ብሶትን መተንፈስስ አንድ ነገር አይደል። ግን አላደረገዉም፡፡ በጣም ታዘብኩት አዘንኩበትም፡፡ ለነገሩ ተስፋየ ቀደም ብሎ ከኮ/ል ታደሰ ሙሉነህ ጋር ቅርበት ስላልነበረዉ ምንተዳየ ብሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ተስፋየ ኮ/ል ታደሰን ለምን አልቀረበዉም ለሚል ጠያቂ ምላሼ የሚሆነዉ ኮ/ል ታደሰ በነኮ/ል ፍፁምና ህግደፍ ከኢ.ህ.አ.ግ. አመራርነቱ ታግዶና ከአስመራና ኤርትራ እንዳይወጣ የታገተ መሆኑን አሳምሮ ስለሚያዉቅ ነበር፡፡ ታዴ ስራ ተነፈጎ፣ ሰዉ እንዳይቀርበዉ እየተደረገ (በተለይ ከዉጭ የሚመጡ ኢትዮጵያዉያን) በዚህ ሁኔታ ተከታታይ ስድስት የግፍ ዓመታትን ገፍቱዋል፡፡(ዝርሩን እንተወዉ ላሁን)። ሰንበትበት ብሎ ታዲያ የኢትዮጵያን ሪቪዉ አስመራ ቢሮ ሳይከፈት በእንጥልጥል ላይ እያለን እነኤልያስ የኮ/ል ታደሰን መታሰር የሚቃወም ህልዉናዉንና ባስቸኩዋይ እንዲለቀቅ እንዲሁም የሁለቱን ህዝቦች ግንኙነቶች ስለሚያበላሽ ጉዳዩን እንዲያጣሩ የሚጠይቅ ጠንካራ ደብዳቤ ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ መላካቸዉን ሰማን፡፡ ኢትዮጵያን ሪቪዉ በድረገፁ አስነበበን ፡፡ የነ ኤልያስ ደብዳቤ በጉዳዩ ላዘንንና መተነፈስ ላልቻልን ወገኖች በጣም ደስ ያሰኘ የአቋም መግለጫ ነበር፡፡ ከኤርትራዊያን አልፎ በእነግድነት የተጠለሉ ኢትዮጵያዉያንን እንዳሻቸዉ በግፍ መግደልና ማፈን ለለመዱት ለኢሳያስ ለነ ኮ/ል ፍፁምና መሰሎቹ ህግደፎች ደግሞ ያልጠበቁትና አስደንጋጭ ፡፡ ያዉም ቤተኛ

ሆኑዋል አጥምደናቸዋል ብለዉ ከተማመኑባቸዉ እነ ኤልያስና ኢትዮጵያን ሪቪዉ፡፡ የተለያዩ ወገኖች በህግደፍ ላይ ያሰሙት የተቃዉሞ መግለጫዎች ለጊዜዉ መፍትሄ ባያስገኝምና እነኮ/ል ታደሰንና ሌሎች ወገኖቻችንን ፈጥኖ መታደግ ባይቻልም ልብ ላለዉ ልብ እንዲል አድርጉዋል እላለሁ፡፡ የእባብን ተናዳፊነት ለማረጋገጥ መነደፍን ለመረጠ ግን ምርጫዉ ከእርሱ ነዉ፡፡

...........

የሆነዉ ሆና ተስፋየ ገ/አብ የኤልያስ ኢትዮጵያን ሪቪዉን ቢሮ በአስመራ መከፈት አይሳካም ሲል ቀድሞ ያመላከተኝን፡ ትንቢት ልበለዉ ሙዋርት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሌ/ኮል አለበል የመሰረተዉ የአማራ ንቅናቄ ሀይል ከህግደፍ ጋር መላተሙና አመራሮቹ በህግደፍ መታገታቸዉ እነደማይቀር እንዲሁም ከነዳዉድ ኢበሳ ኦነግ አፈንግጦ ኒያላ ሆቴል ላይ የኦሮሞ ድርጅት መስርቶ ከህግደፍ እዉቅና ዉጪ ከዉጪ ወገኖች ጋር ግንኙነት የመሰረተዉ ሌ/ኮል አበበ ህይወቱ አደጋ ላይ መንጠልጠሉን መሀላቸዉ ቁጭ ብሎ ሲፍለቀለቅ የነበረዉ ተስፋየ አያዉቅም ነበር እንበል? (አፋኞቹ እነ ኮ/ል ፍፁም እኮ ወዳጆቹ ናቸዉ)፡፡ ኮ/ል ታደሰ ሙሉነህን በሩቅ ሲሸሽ የነበረዉስ ሳይከራርም በህግደፍ ደብዛዉ መጥፋቱ ስለማይቀርና እነ ኮ/ል ፍፁም ኮ/ል ታደሰን ከታሪክነት መፋቅ እነደሚሹ ስለሚያዉቅ ከጠፊ ጋር ላለመታየት አልነበረምን?

የዳዉድ ኢብሳን ኦነግ በግልፅ ተቃዉመዉ የወጡት እነ ብ/ጄል ከማል ገልቹን ብ/ጄል ሀይሉ ጎንፋ አቶ ዮናታን ዲቢሳን በሩቅ ሲሸሽ የነበረዉ ሰነባብተዉ የቁም እስረኛ መሆናቸዉ እንደማይቀርና ሰራዊታቸዉ በህግደፍ እንደሚዘረፍ ወፊቱ ትነግረዉ ነበር ወይንስ ባጋጣሚ ነው ብለን ደጋግመን ደጋግመን እንድናማዉ እንገደዳለን፡፡ ከሌኮ/ል አለበልና ሌ/ኮል አበበ መሀል ቁጭ ብሎ እያዉካካ ታሪካቸዉን ዘርፎ ለሱ አጀንዳ ለሚቀርፁለት ህግደፎች እነደሚስማማ አድርጎ በርዞና ከልሶ ከፃፈዉ በሁዋላ (አሁን አሁንማ የተስፋየ ፅሁፎች ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ የመሆናቸዉ ነገር ተባነነበት) ከአጠገባቸዉ መራቁስ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? ወረተኛነት....ብቻ እነዚያ ወገኖቼ ግን "በሬ ካራጁ ይዉላል" እንዲሉ ነበሩ፡፡

...........

ከኒያላ ሆቴል ሁለት ወጎችን እንካችሁ ልበል፡፡ አንድ አመሻሽ እንደተለመደዉ ኒያላ ሆቴል ጎራ አልኩ፡፡ ተስፋየ ገብረአብ በሌኮ/ል አለበል በሌ/ኮል አበበ ገረሱና ሌላ ከዚያ በፊት አይቻት የማላዉቅ ልጅ ተከቦ ጨዋታ ደርቱዋል፡፡ ጠረጴዛዉ በምግብና መጠጥ ተሞልቱዋል፡፡ ያለ ወጪ ሀሳብ ይበላል ይጠጣል፡፡ ከፋዩ ተስፍሽ ነዉ፡፡ ተስፋየን በእንዲህ ዓይነት ምሽቶች ማግኘትና ማየት የተለመደ ነዉ፡፡ ተስፋየ ገና ስገባ ሲያየኝ ጠራኝና "ስለ መፅሃፉ አስተያየትህን ንገራቸዉ" አለኝ፡፡ ያን ሰሞን የቡርቃ ዝምታን ሰጥቶኝ እያነበብኩት ነበር፡፡ የዛሬዉ የጨዋታ ሀድራ በዚሁ መፅሀፍ ዙሪያ መሆኑ ገባኝ፡፡ "እ ስለዛ ቆሻሻ መፅሃፍህ ነዉ የምትለዉ?" ስለ ቃሉ ይቅርታ መፅሃፍህን ነዉ ያልኩት፡፡እንደምንም አንብቤ ስጨርሽ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ኢትዮጵያና ህዝቡዋን እንደማትወድ ነዉ፡፡ ቂመኝነት የተጠናወተዉ መፅሃፍ ነዉ፡፡ በድጋሚ ይቅርታ ተስፍሽ" በቅፅበት የወረድኩበት ምላሽ ነበር፡፡ ሌ/ኮል አለበል ዘሎ አቅፎ ሲስመኝ ያስተዋልኩት ነገር የአማራ ተወላጁን ሌ/ኮል አለበልን እና የኦሮሞ ተወላጁን ሌ/ኮል አበበን በመሀል ዳኝነት እያከራከረ እንደነበረ ነዉ፡፡ ተስፋየ ምላሼን ከቁብ ሳይቆጥር በሳቅ ይንከተከት ገባ፡፡ ቀጠለ፡፡ በሌ/ኮል አበበ አስተያየትም ይስቃል በሌ/ኮል አለበልም ይፍልቀለቃል፡፡ በወቅቱ የተሰነዘሩትን የሁለቱን ወገኖች ሀሳብ እንተወዉና ምንም በሳቅ የሚያፍለቀልቅ ነገር በሌለበት ሁኔታ የተስፋየ መንከትከት ይብስ አበሸቀኝ፡፡ ከሁለቱም ወገኖች እኔን ጨምሮ "ታሪክን ጠልቀን ባናዉቅም ጥላቻና ቂምን በታሪክነት መፃፍ አንዳችም ጠቀሜታ የለዉም" የሚል ሀሳብ መሰንዘራችንን አስታዉሳለሁ፡፡ ተስፋየ ግን እንዴት እየተረዳዉ እንደነበር አላዉቅም ይስቃል፡፡ "ተስፋየ የቡርቃ ዝምታን በተመለከተ ባስመራ ዩኒቨርሰቲ የታሪክ ረ.ፕሮፌሰር ተከስተ መላኬ ጋር ተወያይቸበታለሁ፡፡ ( ነፍሱን ይማረዉና በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ መምህር የነበረዉና በሁዋላም ተባርሮ በአስመራ ዩኒቨርስቲ ያስተምር የነበረዉ ተከስተ መላኬ የልብ ወዳጄነና ጉዋደኛዬ ነበር ) እናም ተከስተ "እኛ የታሪክ መምህራን እንኩዋን በታሪክ ዉሰጥ የተስተናገዱ አሰቃቂ ኩነቶችን ለአዲሱ ትዉልድ ጥላቻና ቂምን በሚያሰርፅ መልኩ አናስተምርም" ነበር ያለኝ፡፡ አንተ ግን ይሄዉ የስነፅሁፍ ችሎታህን በመሳሪያነት ተጠቅምህ እዚህ ትዉልድና መፃዒዉ ትዉልድ ላይ ጭምር የመረረ ጥላቻና ቂም መዝራት ይዘሀል፡፡ ታሪክን ለታሪክ ምሁራን ብትተዉላቸዉ ደግ ነበር፡፡ አንተ ግን ጭራሽ በዚህ ተግበርህም ይሄዉ ትፍለቀለቃለህ ፡፡ ደግነቱ ህዝቦች ታሪካዊ የፍቅር ትስስራቸዉን በሰከነ ልቦናቸዉ ስለሚያዳምጡ ያንተን መርዝ እነዳለ አይጋቱም" በስሜት ተዉጨ ነበር የወረድኩበት፡፡ ተስፋየ እኔና ብ/ጄ/ል ከማል ገልቹ ሆነን በሳቫና ሆቴል ባደረግነዉ ቆይታም በተመሳሳይ መልኩ ነበር የወረድንበት ልናርመዉ የሞከርነዉም፡፡ ነገር ግን "ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይልቅም" እንዲሉ ተስፋየን የተጠናወተዉ አለቀቀዉም፡፡ ዓገብ! ይላሉ ኤርትራዊያን፡፡ ይብቃ! እረፍ! እንደማለት ነዉ፡፡ ዓገብ ተስፋየ!

.............

በሌላ የኒያላ ሆቴል ምሽት እንደወትሮዉ በክብ ጠረጴዛ ስናዉካካ አመሸንና ወደ ቤት ለመሄድ ተያይዘን ወጣን፡፡ ያኔ ተስፋየ ከሳቫና ሆቴል ለቆ ቴራቮሎ አፓርትማ ገብቶ ነበር፡፡ የኔም ቤት በተመሳሳይ አቅጣጫ ስለሆነ እግረመንገዳችንን እያወጋን ለመሄድ ነበር አወጣጣችን፡፡ ተስፋየ በጣም ሞቅ ስላለዉና እንግድነቱም አለ ልሸኘዉ መረጥኩ፡፡ዉነት ለመናገር ይፈራልም፡፡ በሞቅታዉ ብዙ ያወራ ነበር፡፡ በመሃል "ካሁን በሁዋላ ምን እንደምመኝ ታዉቃለህ?" ሲል ጠየቀኝ፡፡ "ምን ትመኛለህ ?" "ፀጥ ረጭ ያለ ቦታ ነዉ እምፈልገዉ" ምን እያለ ነዉ በሚል ተገርሜ "ምን ማለትህ ነዉ?" ቀጠለ ፍላጎቱን "ትላንትና ሀዝሀዝ ቤተክርስቲያን የማዉቀዉ ሰዉ ዘመድ ሞቶ ቀብር ሄጄ ነበር" አለኝ፡፡ ተስፋየ ያየዉ ሀዝሀዝ የቀብር ስፍራ በአስመራዎች የሙዋች አገር ሩቅ ከሆነ እና ካልታወቀ ሰዉ የሚቀበርበት ቦታ ነዉ ይባላል፡፡ ከፍታ ላይ የሚገኝ ስፍራ ነዉ፡፡ ተስፋየ ቀጠለ "እናም ቦታዉ በጣም ፀጥታ የነገሰበት ነዉ፡፡ ስለዚህ እኔም እዚያ ቦታ አንድ ሜትር በሶስት ሜትር ቦታ ከሰጡኝ ጉድዋዴን ቆፍሬ ለዘላለሙ በፀጥታ ማንቀላፋት እመኛለሁ፡፡ እዚያ ያለዉ ፀጥታ ኡህህህ..." አለና በስሜት በተመስጦም ጭምር ተነፈሰ፡፡ ጠላታችሁ ክዉ ይበል ክዉ ነዉ ያልኩት፡፡ ሰዎች በሞቅታ የተለያየ ባህሪ እንደሚያሳዩ እናዉቃለን የተስፋየ ግን በተብራራ መልኩ ነዉ ምኞቱን የገለጠዉ፡፡ እንዴ ይሄ ልጅ ምን ሆነ? ሞት እመኛለሁ ይላል እንዴ! ቦታዉ ፀጥታ የነገሰበት ነዉ ይላል እንዴ ደሞ! ሙዋቾች ሰፈር ፀጥታ ያልነገሰ ታዲያ የት ይንገስ? ሰዉ በዚች ምድር ሲባክን ኖሮ እስኪ ሲሞት እንኩዋን በፀጥታ ይረፍ እንጂ፤

ይሄ ምኑ ይገርማል? በጣም ፈራሁ፡፡ራሱን ሊያጠፋ ነዉ እንዴ ይሄ ልጅ? አዘንኩለትም፡፡ በዚህ ሁኔታ ብቻዉን ልተወዉ ስላልመረጥኩ ወሬ አስቀይሬ በቀስታ እያዘገምን ቤቱ አስገብቼዉ እስከ እኩለሌሊት እስኪጠጋ ደረስ ቆይቼ መረጋጋቱን ካረጋገጥኩ በሁዋላ ተመለስኩ፡፡ ተስፋየን ተሰናብቼዉ ወደ ቤቴ ሳዘግም እሱን ላረሳሳ ሞከርኩ እንጂ እኔ ግን ከምሽቱ ዉጥረት አልተላቀከኩም ነበር፡፡ደጋግሜ የማብሰለስለዉም “ዉስጡን የሚረብሸዉ ነገር ኖሮ ከዚሁ ሽሽት ይሆን ዘላለማዊ ፅጥታን የተመኘዉ” እያልኩ ነበር፡፡ ኦሮማይ ተስፋየ!

ሰላምና ፍቅር ለአባቴና እናቴ አገር ህዝቦች !!!

በፍቅር ላይ የተመሰረተዉን ዉህደታችንና አንድነታችንን እመኛለሁ!!!

ሠናይ ገብረመድህን (ጋዜጠኛ)
አዉስትራሊያ፣ሜልበርን

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
December 20, 2014